"የመዳን መንገድ ምሳሌያዊው "

እግዚአብሔር መውደቀን አይቶ ያዘጋጀልኝን በግኑ ተመለከትኩ ፤እግዚአብሔርም ፍጡሩን ትተህ ፤ማሳበብህንም ትተህ ፤ምክንያት መደርደርህንም ትተህ ፤በቁስ መደቅም ትተህ ፤አሁን እኔ የሚሰጠውን ተቀበል!! እንዳለኝም ተረዳሁ ።

የተሰጠኝ ተስፋ አልተፈፀመም ፤የሔዋን ዘሪ ለአባብ ራሱን ስቀጠቅጥ አላየሁም ፤ይህ ተስፋ ሙሉ በሙሉ እስከሚፈፀም ድረስ እግዚአብሔር ያሳየኝን መስዋዕት #ምሳሌዊን ማቅረብ ጀመርኩ ፤

መስዋዕትንም አቀርባለሁ ፤ለልጆቼንም አስተማርኩ።ልጆቼ ግን መስዋዕቱ ወንድ ልጅ እስከሚመጣ እንደሚሰዋ አላወቁም ፤እግዚአብሔር የእነሱን።ልባቸውን እንደሚፈልግ አልተረዱም ፤ ዓላማውን ባለመረዳት በክፋት ተነሳስቶ አንደኛው ሌላኛውን ገደለው ፤እንቅርት ላይ ጆሮ ድግፍ ይህ አይደል ? ።እኛ ማ "ካንቺ የሚወለደው ወንድ ለአባቡ ራሱን ይቀጠቅጣል" ስባል ወንድ ልጅ ስናገኝ ።የድብያብሎንስ ተበቃይ አገኘን ብለን "ወንድ ልጂ ይህ ነው ከእግዚአብሔር አገኘሁ " አለን (ቃየንን)።ግን ምን ያረጋል እባብን ይቀጠቅጣል ብለን ስንጠብቅ ወንድሙን ቀጥቅቶ አረፈው ፤

ለካ ተስፋው ሩቅ ነው፤ቅርብም ነው፤በእኛ ሳይሆን በእሱ ነው የሚዘጋጀው ፤ወይ አለማስተዋል ።እግዚአብሔር #ከዘራችሁ ወንድ ልጅ ይገኛል አላለም፤ምን ሆኜ ነው ግን ወንድ ልጅ #ከዘሪዋ_ብቻ እንደሚገኝ ያልተረዳሁት? ።ስለዚህ አሁንም ተስፋዬ ሙሉ ነው።ከእግዚአብሔር የሚገኘው ወንድ ልጅ ከዘሪዋ ብቻ የሚገኝ ነው።በዚህ ልጂ {ቃየን}ጥፋት ተስፋ አልቆርጥም ።

እያረጀው አይደል ? የፈጠራቸው አምላክ እንዳለ ይወቁ ዘንድ ለቀሩት ልጆቼ አሳወኩኝ። እሱም ብሆን መቼ ጨቅኖ ይተዋል፤በፍጥረቱ በኩል እየገለጠ ።ራሱን ማሳወቁን አይተውም።ልጆቼ ግን በጎጢአት በመወለዳቸው መልካሙን ማድረግ አልቻሉም ።በክፋት ሄዱ ።ለእኔ ብሎ የገባውን ቃል አስቦ አሁንም ወንድ ልጅ ራስ ራሱን የሚቀጠቅጥ እስከሚመጣ ድረስ አንድ ጻድቅ ከተገኘ ።አንደ ይነጥቃል ፤አንደ ያተርፋል ፤አንደ እንድሁ ምህረት ያደርጋል ።ይህን ሁሉ ተስፋ ስለሰጠኝ ላልተወኝ፤ስለወደደ ከእኔ ጋር ወደቀ እኔን ለማንሳት ፤ሁለም ብሆን ፈጽሞ እንዳልጠፋ ይጠብቀኛል ።

በጎጢአት ተፀንሼ እንደት መልካሙን ላድርግ ? ተስፋ የተጣለበት ወንድ ልጅ ሳይህገኝ እንዴት አባትም ቸል ይበለን?እኔ ባልታመን እንኳ እሱ ታምኖ ይኖራል ። አሁንም አይተውም፤ወንድ ልጅ እስከምመጣ ድረስ ለጊዜው ከጊዜያዊ ቁጣ ለመትረፍ ፤ለመቆየት፤እግዚአብሔርን እያመለኩ፤የእንስሳት መስዋዕትም እየሰጠው ቆያለሁ።

ብዙ መስዋዕት ተሞከረ ፤እንዱም ፍጹም ልያደርግ ልያድን እንደማይችል አውቃለሁ ።ምንም የማያውቀውን ብላተና ልሰዋው ተነሳሁ ፤እግዚአብሔርም "አንተ አታዘጋጀም" በማለት ራሱ በዕዕ ሳበቅ የተያዘጅውን በግ አሳየኝ ፤እንዴትስ እምብ ልበል እሱ የሚሻለውን፤ የሚልቀውን፤ፍጹምን፤ያውቃልና ።እኔም

ከልጄ አንገት ሰፈይን መለስኩ ፤አሁንም ወደ ራሴ፤ወደ አካባብዬ እንዳላይ እግዚአብሔር አስተምሮኛል፤ አሳምኖኛል።እርሱ የሰጠውን ተስፋ እጠብቃለሁ ....

አንዷን ትዕዛዝ እንኳን መቋቋም ባማልችለው ደካማው በእኔው ላይ ስለጥፋቱ 10 ትዕዛዝ ሰጠ፤መጀመሪያምውኑ ሕግ መቼ አነስና?በህልናዬ ያተመው የእርሱ ሕግም አለና።ይህም እያለ በጹሑፍ የተጻፈውን ሕግን ብያይ ጎጢአት ይተዋል ብሎኝ በጹሑፍ ሰጠኝ።ይህ ሕግማ በደሌን አሳይቶኛል ፤በዚህ ተጠቅሞኛል ግን ከበደል ነፃ አላረገኝም።ሕጉንም ጠብቀ የሕግ አስተማሪ፤የሕግ አስከባሪ ብሆን እንኳን ይህ ፅድቁ ፡ፅድቅ ሆኖ የማይቆጠር #መርገም ተባለልኝ ፤

ቁራ ቁራ የሚል ቤተመቅደስ ሸልቶኛል ፤ ቁራ ቁራ ብሎ እንኳን ከፍርድ ህልናዬን ብያነፃ መልካም ነበር።ነገርግን አገልግሎቱም የገማች፤ የሚትገማ ፤የማትጠቅም እንደሆነች ምሳሌያዊው እንደሆነ አውቃለሁ ::

የሐዋን ዘሪ የአዳም ዘረ መል የሌለው ከመንፈስ ቅዱስ የተፀነሰ ወንድ ልጁ በዘመኑ መጨረሻ መወለዱ ተሰማ ፤እሰይ አሁን የብርሃን ፍንጣቀው ፡ጮራው ይታየኛል ፤ፍጹም የሰውን ስጋ ስለለበሰ አገልግሎቱን እስከምጀምር ሰይጣን እንኳን በቅጡ ወንዱን ማወቅ አልቻለም ፤የምን አገልግሎቱን ጀምሮ ? ከጀመረ በኃላ እንኳ መቼ አወቀው፡አዳኝ እንደሆነ እንዴት እንደሚያድን መቼ አወቀው ? ለእባብ ማ የማይፈታ እንቆቅልሽ ነው።

ይህም ወንድ ልጅ የእባብ ራስን ለመቀጥቀጥ የእኔን ውርደት ለራሱ ወሰደ ፤እባብም የጨረሰው መስለውት የውርደት፣የወንበዴ ሞት እንድሞት አቸከለ፤በመሞቱ ራሱን ሳይቀጥቀጥ የሚያመልጥ የምተርፍ መስለውት፤አንዳንደ እባብ እንኳ ሳያውቅ #ተበቃየን ያገለገለ ይመስለኛል ::ሞኝ ፣ደካማ ፣የማይነሳ ፤ የሚታለል መስሎ አሸነፈ ፤በድል ተወጣ፤የመዳን ቀንደ ነውና ::

ይህ ወንድ ልጅ ለእኔ ከአብ ጋር ተስማማ ፡ለመሞት ::ግን የጴጥሮስን ምክር ሰምቶ ባይሞትስ? መና ሆኝ ቀርቼ ነበር፤የእናቱን እምባ አይቶ ከመስቀል ብወርድ ምን ይውጠኝ ነበር? ስለእኔ ባይጮህ፤ባያለቅስ፤ባይለምን ፤ማን ይለምን ነበር? ማንም የለም።

ይህ ነው በግ ፤ይህ ነው ቤዛ ፤ይህ ነው ልመናው የተሰማለት ፤ይህ ነው ወንድ ልጅ ፤ይህ ነው የከሴትቷ የየተገኘ ዘሪ፤እሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

አሁን መቅዱሱ ደም ደም ማለቱ ቀረ በኢየሱስ ደም።አመድ ተቀብቼ ነፃውት ማለትም ቀረ፤ሙሉ በሙሉ ወደ ክብረ ወደ ማንነቱ ተመለስኩ በእርሱ ስራ፤ያሁሉ የፈሰሰው የእንስሳት ደም አበቃ በኢየሱስ ደም ለዘለዓለሙ ነፃ ሆንኩ ፤እባብም ተሸነፈ፤ተቀጠቀጠ ፤ኢየሱስ ሁሉንም ተቆጣጠረ ፤::አሁን የሰማያት ጌታ የሁሉ አምላክ የእኔ ጌታ በእኔ ላይ አደረ ......

የህልና ሕግ እያለ እንኳን ፤አንድ ትዕዛዝ ብቻ ተጨምሮ፡መታዘዝ ተስኖኝ ወደኩ፤አሁንም 10 ሕግ ተጨመረ ፤ደግሞም የሽማግሌዎች ወግም አለ።ይህ

ሁሉ ወደ ቦታዬ ልመልሰኝ እንደማይችል ተረዳሁ ::

እኔ የጠበቁት ተስፋ ያደረኩት ወንድ ልጅ ሌላ አድስ ሕግ ፤አድስ ወግ አልጨመረልኝም፥ነገርግን ፅድቁን አደርግ ዘንድ አቂም ፤ጉልበት ሰጠኝ::የሚጠበቀው ይህ ነው አቅም ሰጠኝ ::ኢየሱስ ::

ያኔ በምሳሌያዊው አገልግሎት (በኦሪት) መልካም የሆነውን ሁሉንም ለማድረግ እፈልግ ነበር::ግን ያን መልካሙን የእግዚአብሔርን መልክ የሚያሳየውን ማድረግ አልቻልኩም ነበር::አሁን ግን በእግዚአብሔር ልጅ በኢየሱስ ክርስቶስ ፀጋ (አቂም)ና እውነት አገኘሁ ::አሁን የሚወደውን የአምላክን ትዕዛዝ እፈጽማለሁ ::

ምንም እንኳ ቆመ የሚሄድ ብሆንም እንኳን ፤የሚናገር፤የሚጽፍ ፤የተማርኩት፤ፍደል የቆጠርኩት ብሆንም እንኳን ፦እኔ ራሴን ለእግዚአብሔር ምርጥ እቃ በራሴ ብቃት ማድረግ እንደማልችል ተረዳሁ ::

ስለዚህም በናፍቆት የሚጠባበቀው፦አካሉ ኢየሱስ መጥቶልኛል::ለግዜው የተሰጠውን #ምሳሌያዊ አገልግሎት ላይ አልቆምም ፤ሳልበርዝ ማለትም ከኦሪት ግማሽ ከአድስ ግማሽ ሳልል፦በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ሆነው ወደ መርጨት ደም በእምነት መጣሁ (ኑ)::ኢየሱስ ለሁሉም ፈውስ መድኃኒት ነው:: አዎ ኢየሱስ አድኖኛል::ኢየሱስ ያድናል ተስፋም ያደረኩት እሱን ብቻ ነውና አደነኝ::ኢየሱስ ያድናል ስል፦ "ስለ ቆዳ ቁስል ብቻ ሳይሆን ስለሁሉም ነገር ብቸኛ ፈውስ ነው እያልኩ ነው::

ከምሳሌያዊው(ከኦርቱ) ወደ አካሉ ደረስን ::ያዳነን፤አቂምን የሰጠን፤ይባረክ::

" ሃሌ ሉያ "

"አትስረቅን፤አታመንዝርን፤በሀሰት አትመሰክርን ....፤መፈፀም አልቻልኩም ነበር::አሁን በኢየሱስ ክርስቶስ ፀጋ ትዕዛዝን ለመፈጸም አቂም አገኘሁ ::"

ማንም ይሁን ማንም ለእግዚአብሔር ራሱን አሳልፎ ስሰጥ እግዚአብሔር ምርጥ እቃ አድርጎ ይሰራል፤ከዚያም ጎጢአትን እንደሚያቻችል ሳይሆን #እንደሚያስጥል ተረዳሁ ::

በሀልናችንም በጹሑፍም የነበረውን ያለውን ትዕዛዝ ለመፈጸም የሚያስችል፦ከእኔ የሆነ አንዳች አቂም የለም::አለማዊ ምኞትን የሚያስጥለው የእግዚአብሔር ፀጋ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው::

በእግዚአብሔር ልጅ በኢየሱስ ክርስቶስ የሆነው ፀጋ አድኖኛል:: በቅድስናም እንኖር ዘንድ ፀጋው ብቻ ከኃጢአት ያርቀኛል::ከእኔ የሆነ ቅድስና የለም::

"ከፀጋ በታች ነኝ" ስል፦ትዕዛዝን በመፈጸም፤በቅድስናም እንድመላለስ የሚያደርገው፤ አቂሙ ፦እርሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው እያልኩ ነው::

ከእኔ በሆነ ጥረት ምርጥ እቃ መሆን፤በቅድስና መመላለስ የለም::

ከእርሱ ስሪ በመሆን ነው:: በፀጋው ብቻ ነው::

ከየትኛውም በደል ኃጥአት እሸሻለሁ ብል፦ከእኔ በሆነ አቂም መሸሽ አልችልም ::እንድሸሽ የሚያደርገው፤አቂም የሚሆነልኝ የእግዚአብሔር ፀጋ ብቻ ነው::

ፀጋ ፦ፀጋ ነው የሚያስብለው በእግዚአብሔር ችሮታ ሙሉ በሙሉ በመሠራቱ ነው እንጂ ከእኔ አንዳች ነገር ተጨምሮ አይደለም ::

እድሉ ዮሐንስ ጋምሳ
ተባረኩ